

# ዓለም አቀፍ የባህሪ ቴራፒስት

# መስፈርቶች



ዓለም አቀፍ የባህሪ ትንተና ድርጅት 2021 v100

# የተረጋገጠ የዓለም አቀፍ የባህሪ ቴራፒስት ለመሆን የሚያስፈልጉ መስፈርቶች 01

የዓለም አቀፍ የባህሪ ቴራፒስት (ዓ.ባ.ቴ) በባህሪ ተንታኞች የተነደፉ የባህሪ ትምህርት፣ ድጋፎች እና አገልግሎቶች በመደበኛነት ተግባራዊ በሚያደርጉ ሰዎች የሚወሰድ የብቃት ማረጋገጫ ነው። የዓ.ባ.ቴ መስፈርቶች በአምስት ሰፊ ምድቦች ይከፈላሉ። እነዚህም ምዝገባ፣ የትምህርት መስፈርቶች ማጠናቀቅ፣ ክትትል የሚደረግበት ልምምድ፣ የእጩዎች ክህሎት ፈተና እና የዓ.ባ.ቴ የኦንላይን ፈተናን ማለፍ ናቸው።

ወደ www.theibao.com ይሂዱና የእጩ መለያዎን ይፍጠሩ።

ይመዝገቡ፥ ክፍያዎችንም ይክፈሉ

ከዓ.ባ.ቴ የትምህርት ይዘት የ40 ሰዓት ሥልጠና ያጠናቅቁ

የ300 ሰዓታት ክትትል የሚደረግበት ልምምድ

የእጩዎች ክህሎት ፈተና

የዓ.ባ.ቴ የኦንላይን ፈተና

# የተረጋገጠ የዓለም አቀፍ የባህሪ ቴራፒስት ለመሆን የሚያስፈልጉ መስፈርቶች 02

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ**

(ወይም ክልላዊ አቻ)

**በዓ.ባ.ተ.ድ ይመዝገቡ፥ ክፍያዎችንም ይክፈሉ**
**የስነምግባር ስምምነት ቅጹን ይፈርሙ**

የተሟላ የ40 ሰዓታት
የጸደቀ የስልጠና ይዘት

ተቆጣጣሪን ይምረጡ እና
የተቆጣጣሪ ስምምነትን
ይፈርሙ

የተሟላ የእጩዎች
ክህሎት ፈተና

የ 4 ሰዓታት ተከታታይ
ትምህርት ያጠናቅቁ

የ 300 ሰዓታት ክትትል
የሚደረግበት ልምምድ
ያጠናቅቁ

የ10 ሰዓታት የተቆጣጣሪ
ክትትል ተቀበል

የዓ.ባ.ቴ ፈተናን ማለፍ

# የ40 ሰዓት የዓ.ባ.ቴ የስልጠና ይዘት



ለዓ.ባ.ቴ ፈተና ለመቀመጥ የዓ.ባ.ቴ የሥልጠና ይዘት ያስፈልጋል። የተረጋገጠ የዓ.ባ.ቴ ሆነው ሙያዎን ለማከናወን የሚየስፈልጉ የዓ.ባ.ተ እና ተያያዥ መረጃዎችን ያለው ቢያንስ 40 ሰዓት ያለው ይዘት ነው። የሥልጠናው ይዘት ለሚከተሉት ርዕሶች ተዛማጅ የሆኑ መረጃዎች የያዘ ነው፡-


- ጉዳቶች
- የባህሪ መሠረታውያን
- መረጃ አሰባሰብ
- በግምገማ ሂደቶች እገዛ
- የማስተማር ክህሎቶች
- አስቸጋሪ ባህሪያት
- ሙያዊነት

ለጥናት የሚያስፈልጉት ክህሎቶች እና ፅንሰ-ሀሳቦች በዓ.ባ.ቴ የሥልጠና ይዘት እና በዓ.ባ.ቴ የተብራራ የሥልጠና ይዘት ሰነድ በዓ.ባ.ቴ.ድ ድረ-ገጽ ላይ ለመውረድ ቀርበዋል፡- www.theibao.com.

ይህ የ40 ሰዓት ሥልጠና ምንም እንኳ በአብዛኛው ማንኛውም አቅራቢ ሁሉንም መረጃ ቢያቀርብም ከተለያዩ ምንጮች ማግኘት ይቻላል።  ከአንድ በላይ አቅራቢ በሚጠቀሙበት ጊዜ ከሌላ ያገኛችሁት እና የነበራችሁን ይዘቶች መደጋገም እና ተጨማሪ ሰነዶችን ማብዛት የማስከተል ስጋት አለው።

ሥልጠናው ምንም እንኳ በ1 ሳምንት ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ ቢቻልም ለሥልጠና የተለመደው ጊዜ ከ2 እስከ 10 ሳምንት ነው።

አንዴ ከተጠናቀቀ በኋላ እጩው የ40 ሰአት ስልጠና ማጠናቀቂያ ማረጋገጫውን በኦንላይን መለያቸው ውስጥ ማስገባት ይጠበቅበታል።



# የተቆጣጣሪ መስፈርቶች

04

እንደ ተቆጣጣሪ ሆነው የሚያገለግሉ የባህሪ ተንታኞች በዓ.ባ.ተ እድገት፣ በየተተገበረ የባህሪ ትንተና መስክ እና በዓለም ዙሪያ ደግሞ እያደገ እየመጣ ያለውን የዓ.ባ.ቴን መለማመድ ምን ማለት እንደሆነ ግንዛቤ ማስጨበጥ ላይ ትልቅ ሚና አላቸው። አንድ ተቆጣጣሪ በከፍተኛ ክትትል፣ በስነምግባራዊ ምሪት እና በሰፊ እውቀቱ ነው ዓ.ባ.ቴ እንዲያድግ የሚረዳው።

ዓ.ባ.ተ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በተለያየ ፍጥነት እያደገ ስለሆነ፥ አንድ አይነት የተቆጣጣሪ መስፈርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚገኙ ለሁሉም እጩዎች ሊሆን አይችልም። በመሆኑም የዓ.ባ.ተ ድርጅት ለዓ.ባ.ተ እጩ ተቆጣጣሪ ለመሆን ነፃነትን እና ብቃትን በጠበቀ መልኩ የተለያዩ አማራጮችን ፈጠሯል።

# በተለይም ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶች

<u>የዓ.ባ.ተ.ድ ተቆጣጣሪዎች በተለይም ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ በአጠቃላይ ካሉት ከተቆጣጣሪዎች የ10% የሚሆን የተቆጣጣሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃዎች ኦዲት ይደረጋሉ።</u>

አንድ ተቆጣጣሪ ከሚከለተሉት ቢያንስ <u>አንዱን</u> የግድ ማሟላት አለበት፡-

1. መልካመ ስም ያለው ዓ.ባ.ተ
2. ከሌላ የማረጋገጫ ቦርድ ወይም አካል መልካም ስም ያለው የባህሪ ተንታኝ (ለምሳሌ፡- BCBA®፣ BCBA-D®፣ QABA®፣ እንደ ባህሪ ተንታኝ የግዛት/ክልላዊ/ብሔራዊ ፍቃድ)
3. ከABAI እውቅና ካገኘ ፕሮግራም የማስተርስ ወይም የዶክትሬት ዲግሪ የያዘ
4. በተዛማጅ ዲሲፕሊን የማስተርስ ወይም የዶክትሬት ዲግሪ፣ የዓ.ባ.ተ ተፈላጊ የትምህርት ዓላማዎችን በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ፣ ወይም ተመሳሳይ
5. *የማስተርስ ወይም የዶክትሬት ዲግሪ በዓ.ባ.ተ መስክ ውስጥ 5 ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት ቀጥተኛ ሥራ ከክትትል ልምድ ጋር (*ከፖርትፎሊዮ ግምገማ እና የዓ.ባ.ተ.ድ ተቀባይነት ጋር)

# የዓለም አቀፍ የባህሪ ቴራፒስት የክትትል ስምምነት

ቀን:- ______________________________

ይህ ስምምነት በዓ.ባ.ቴ እጩ (ክትትል የሚደረግለት) እና በተቆጣጣሪው መካከል የሚኖረውን ግንኙነት፣ ሚናዎች እና የሚጠበቁ ነገሮችን ይገልጻል።

የተረጋገጠ ዓ.ባ.ቴ የመሆን ሂደት ውስጥ የተቆጣጣሪ ክትትል በጣም አስፈላጊ ገጽታው ነው። ሂደቱ አስተማሪ ነው ደግሞም ለእጩው ከዓ.ባ.ቴ የ40 ሰዓታት የስልጠና ይዘት ጋር የተጣጣሙ ክህሎቶችን ግልጽ የማስፈጸሚያ እድሎችን እና ልምዶችን ይሰጣል።

አጠቃላዩ ክትትል የሚደረግበት ልምምድ 300 ሰዓት ሲሆን የተቆጣጣሪ ክትትል የሚደረግበት ደግሞ ለእያንዳንዱ የ30 ሰዓት ልምምድ 1 ሰዓት ክትትል ነው። ጠቅላላው ክትትል የሚደረግበት ልምምድ ሰዓት 10 ይሆናል። ይህ 300 ሰዓት በአጭሩ በ10 ሳምንት ወይንም 24 ወራት በሚሸፍን ጊዜ ሊፈጸም ይችላል። **ከተመዘገቡበት ቀን ጀምሮ** ከ24 ወራት በላይ ለሚፈልጉ እጩዎች በዚህ ኢሜይል ሊያነጋግሩ ያስፈልጋል:- info@theibao.com.

ይህ ኮንትራት ከ ______________________ እስከ ______________________ ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል።

የክትትል ሰዓታት ሊመዘገቡ የሚችሉት የክትትል ስምምነት ሲኖር ብቻ ነው። ሁሉም የልምምድ ሰዓታት ወደሚፈለገው ድምር እንዲቆጠሩ በክትትል ግንኙነት ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ለውጦች ወዲያውኑ በዓ.ባ.ቴ.ድ ድህረ ገጽ ላይ እንዲዘምኑ የግድ አስፈላጊ ነው።

ተቆጣጣሪዎች በዓ.ባ.ቴ የተቆጣጣሪዎች ብቃት ዝርዝር ውስጥ የተቀመጡትን መመዘኛዎችን ማሟላት አለባቸው።

ተቆጣጣሪዎች እና እጩዎች ሁሉንም ልማዶችን፣ አገልግሎቶችን እና ቁጥጥሮችን በዓ.ባ.ቴ.ድ የስነምግባር መመሪያዎች መሰረት ማድረግ አለባቸው። ለ10% እጩዎች ለሚሆኑ የተቆጣጣሪዎች የብቃት ኦዲት ይከናወናል። ተቆጣጣሪዎች ከዚህ የክትትል ልምድ ጋር በመስማማት ብቃቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የማረጋገጫ ሰነዶችን ለማቅረብ ይስማማሉ።

የልምድ ወሰን:-

እጩው ከዓ.ባ.ቴ የ40 ሰዓት የሥልጠና ይዘት ጋር የሚጣጣሙ ተግባራትን እና ክህሎቶችን በማከናወን በዓ.ባ.ተ አገልግሎት አቅርቦት ላይ ይሳተፋል። የተቆጣጣሪ ክትትል በአካል በመገኘት በግል፣ በቡድን፣ ወይም በርቀት በመሆን በግል ወይም በቡድን ክፍለ ጊዜዎች ሊከናወን ይችላል።

# የዓ.ባ.ቴ የቁጥጥር ውል (የቀጠለ)

መስፈርቶች፡-

እጩ የክትትል ስራዎችን በመዝገብ መዝግቦ ለመያዝ ተስማምቷል።

ተቆጣጣሪው በተገቢው ተግባራት ላይ ዕጪው የተጠቀመውን ሰዓታትን ለመፈረም ይስማማል ደግሞም ሰዓቱ በአግባቡ ከተከናወነ የክትትል እንቅስቃሴዎችን ፊርማ አይከለክልም።

ተቆጣጣሪ እና እጩ ለእያንዳንዱ የክትትል ስብሰባ የክትትል ሰነድ ቅጽ ወደመለያቸው ለማስቀመጥ ይስማማሉ።

ተቆጣጣሪው የእጩ ክህሎት ፈተና በመስጠት ሁለት የክህሎት ስብስቦችን መርጦ ይገመግማል። ተቆጣጣሪው ለእጩ ክህሎት ፈተናዎች የእጩ የችሎታ ሙከራ ማጽደቂያ ቅጽን ወደ መለያው ያስቀምጣል።

ውሉ በማንኛውም ጊዜ በሁለቱም ወገኖች ሊቋረጥ ይችላል። ነገር ግን የልምምድ ሰአታት ያለአግባብ እንዳይስተጓጎሉ ሁሉንም ልዩነቶች ለመፍታት አስፈላጊውን እርምጃዎች በሙሉ መወሰድ አለባቸው።

እጩው የደንበኛ ጭብጥ፣ መረጃን እና ሚስጥራዊ መረጃን ከተቆጣጣሪው ጋር ለማጋራት የደንበኛ ፈቃድ የማግኘት ሃላፊነት አለበት።

ተቆጣጣሪው ለክሊኒካዊ ውሳኔ አሰጣጥ፣ የጉዳይ መመሪያ እና ተጠያቂነት ሃላፊነት እንዳለበት እጩ እና ተቆጣጣሪው ይስማማሉ። በአገልግሎት አቅራቦት እና በተቆጣጣሪነት ሂደት ውስጥ ለሚከሰቱ ማንኛውን አሉታዊ ሁኔታዎች ዓ.ባ.ተ.ድ ምንም አይነት ተጠያቂነት እንደሌለው ሁለቱም ይስማማሉ።

ሁለቱም ወገኖች በዚህ ሰነድ ድንጋጌዎች እና በዓ.ባ.ቴ.ድ የስነምግባር መመሪያዎች መሰረት ሙያቸውን ለመለማመድ ይስማማሉ።

የእጩ ፊርማ፡- ____________________

የእጩው ስም በፊደል፡- ____________________

የእጩ ኢሜይል፡- ____________________

የተቆጣጣሪው ፊርማ፡-____________________

የተቆጣጣሪ ስም በፊደል፡- ____________________

የተቆጣጣሪ ኢሜይል፡- ____________________

የ300 ሰአታት ክትትል የሚደረግበት አሰራርን ለመጀመር የክትትል ስምምነት በእጩ እና በተቆጣጣሪው መፈረም አለበት። ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ እጩው ክትትል የሚደረግባቸው የልምምድ ሰዓቶችን መመዝገብ መጀመር ይችላል።

# በተቆጣጣሪ ክትትል የሚደረግ ልምምድ

**ለዓ.ባ.ቴ ፈተና ለመቀመጥ ቢያንስ 300 ሰዓታት በተቆጣጣሪ ክትትል የሚከናወን ልምምድ ያስፈልጋል።**

**ለ30 ሰዓታት ልምምድ አንድ (1) ሰዓት የተቆጣጣሪ ክትትል ያስፈልጋል።**

**እንደ ቀጥተኛ የልምምድ ሰዓታት ሊከናወኑ የሚችሉት የሰዓት ብዛት ላይ ምንም ገደብ የለም። ይህ ማለት የዓ.ባ.ቴው እጩው ክትትል የተደረገበት የልምምድ ሰዓት ሙሉ በሙሉ ወይም 100% አገልግሎት ሲሰጥ መሆን ይችላል።**

ለእያንዳንዱ ለ30 ሰዓታት ልምምድ አንድ ሰዓት የተቆጣጣሪ ክትትል ያስፈልጋል። በእነዚህ 30 ሰዓታት በማንኛውም ጊዜ የተቆጣጣሪ ክትትል ማከናወን ይቻላል። ለመጀመሪያዎቹ 30 ሰዓታት ልምምድ (ከ1-30) የአንድ ሰዓት ክትትል ያስፈልጋል፤ ለእጩው ቀጣይ 30 ሰዓታት ልምምድ አንድ ሰዓት ያስፈልጋል (ከ31-60)፤ በዚሁ መሠረት በሚቀጥሉት በእያንዳንዱ 30 የልምምድ ሰአታት (61-90፣ 91-120፣ ወዘተ...) የአንድ ሰአት ክትትል ያስፈልጋል።

የ30 ሰዓታት ልምምድ በ 1 ሳምንት ርዝመት፣ በ2 ሳምንት ርዝመት፣ ወይም ከዚያ በላይ ሊወስድ ይችላል። እነዚህን 30 ሰዓታት ለመፈጸም ምንም ያህል ጊዜ ቢወስድ፥ አንደኛው ሰዓት ግን ክትትል የሚደረግበት መሆን አለበት።

አንድ እጩ በ30 ሰአታት ከአንድ ሰአት በላይ የተቆጣጣሪ ክትትል ማግኘት ይችላል ነገር ግን ከ30ው ሰዓት አንድ ሰዓት ብቻ ለዓ.ባ.ቴ ፈተና ለመቀመጥ ከሚያስፈልገው 10 ክትትል የሚደረግበት ልምምድ ሰዓት ሊመዘገብ የሚችለው።

ሁሉም የክትትል ሰዓቶች በርቀት ዘዴዎች ሊጠናቀቁ ይችላሉ።

ክትትል የሚደረግባቸው የልምምድ ሰዓቶች ከተመዘገቡ እና የተቆጣጣሪውን ስምምነት ሲፈርሙ ወዲያውኑ ሊጀምሩ ይችላሉ። እጩው የ40 ሰዓት ሥልጠናው በመውሰድ ላይ ሳለ እነዚህን ሰዓታት ማጠራቀም ይችላል። ክትትል የሚደረግበት ልምምድ ከመጀመሪያችሁ በፊት የ40 ሰዓት ሥልጠናውን ማጠናቀቅ አያስፈልግም።

# በተቆጣጣሪ ክትትል የሚደረግ ልምምድ (የቀጠለ)

የቡድን ክትትል ከ 10 (50%) ውስጥ ከ 5 ላልበለጠ የክትትል ሰዓቶች ተቀባይነት ይኖረዋል።

የቡድን ክትትል ቢያንስ 5 እጩዎች ላላቸው ቡድኖች ብቻ የተወሰነ ይሆናል።

እጩው በእውቅና/በስልጠና ሂደታቸው ብዙ ተቆጣጣሪዎችን መጠቀም ይችላል።

- **እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ በዓ.ባ.ተ ድርጅት የተመዘገበ** እና የተቆጣጣሪ መስፈርቶችን የሚያሟላ **መሆን አለበት።**
- ክትትል የሚደረግበት ልምምድ ከመጀመሩ በፊት እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ የተፈረመ የተቆጣጣሪ ስምምነት መፈረም አለበት።
- እጩዎች አደገኛ የሆነ የሥነ ምግባር መመሪየዎች ጥሰት ፈጽሞው ከተገኙ ተቆጣጣሪዎች ከእጩው ጋር ያላቸውን የክትትል ግንኙነት የማቆም መብታቸው የተጠበቀላቸው ነው።

# ሰነድ አያያዝ

ለእያንዳንዱ በቡድን፣ በርቀት ወይም ፊት ለፊት ለሚደረግ የክትትል ስብሰባ በሙሉ፣ **ተቆጣጣሪው እና እጩው ክትትሉን ለመመዝገብ የክትትል ሰነድ ቅጹን መሙላት አለባቸው**። እነዚህ ቅጾች ሁለቱም ወደየራሳቸው የዓ.ባ.ተ ድርጅት መለያ በመግባት መሞላት አለባቸው። ክትትል የተደረገበት ሰዓት ወደሚፈለገው ጠቅላላ 10 ሰዓታት እንዲሞላ ለእያንዳንዱ የክትትል ሰዓት የክትትል ሰነድ ቅጽ መሙላት ግዴታ ነው።

እጩው የክትትል ሰነድ ቅጹን በዓ.ባ.ተ ድርጅት መለያ በመግባት ያስገባል። የዓ.ባ.ተ ድርጅት መድረኩ ደግሞ ለተቆጣጣሪው ይልካል፥ ተቆጣጣሪው ደግሞ በመለያው በመግባት የራሱን ድርሻ ይሞላል። ቅጹ ተሞልቶ እና ተፈርሞ ካለቀ በኋላ እጩውም ተቆጣጣሪውም ቅጹን ማግኘት ችላሉ።

የሚፈለገው ሰነድ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

- የክትትል ስብሰባ ቀን
- የሕክምና ቅንብር
- የክትትል ጊዜ የተጀመረበት ቀን
- የክትትል ጊዜ የሚያበቃበት ቀን
- በክትትል ጊዜ ውስጥ የተከማቹ አጠቃላይ የልምድ ሰዓቶች
- በክትትል ጊዜ ውስጥ የተጠራቀሙ አጠቃላይ የክትትል ሰዓቶች
- የተጠራቀሙ ጠቅላላ ሰዓቶች
- የክትትል ዘዴ
- የክትትል አይነት (ቡድን/ግለሰብ/ወዘተ)
- የክትትል ማስታወሻዎች
- አስተያየት

# የዓ.ባ.ቴ የክትትል ሰነድ መያዣ ቅጽ

IBAO International Behavior Analysis Organization

ቀን፡- ____________________

የሕክምና ቦታ፡- ____________________

እጩ፡- ____________________

ተቆጣጣሪ፡- ____________________

የክትትል ጊዜ የተጀመረበት ቀን፡- ____________________

የክትትል ጊዜ የሚያበቃበት ቀን፡- ____________________

የልምምድ ሰዓት በዚህኛው ጊዜ፡- ____________________

ክትትል የተደረገበት የልምምድ ሰዓት በዚህኛው ጊዜ፡- ____________________

የክትትል አይነት (አንድ ያክብቡ)፡- የቡድን የግለሰብ

የክትትል አይነት (አንድ ያክብቡ)፡- በምልከታ በቪዲዮ በግምገማ በስብሰባ

ማስታወሻ፡- ____________________

____________________

____________________

አስተያየት፡- ____________________

____________________

____________________

ፊርማ፡- ____________________

ክትትል በሚደረግባቸው የልምምድ ሰዓታት፥ የእጩው ተቆጣጣሪ በክትትል ወቅት መካናቸውን ማሳየት የሚገባቸውን ሚናዎችን እና ክህሎቶችን መሠረት በማድረግ የሚጠበቅበትን የክህሎት ስብስቦችን መተገብበሩን ለማረጋገጥ የእጩ ክህሎት ፈተና (እ.ክ.ፈ) ያካሂዳል። የእጩ ክህሎት ፈተናዎች ለሁሉም እጩዎች የተለያዩ ሊሆን ይችላሉ። እንዲፈተኑት ቅድመ-ምርጫ የተደረገላቸው የክህሎት ስብስቦች የሉም።
ለፈተና የሚቀርቡ ክህሎቶች ክትትል የሚደረግባቸው ልምምዶች ናቸው። የእጩ ክህሎት ፈተናዎች ለምሳሌ በመረጃ አሰባሰብ፣ በልዩ ሙከራዎች አተገባበር፣ በቋንቋ ማግኛ ፕሮግራሞች፣ በተግባራዊ ክህሎት ፕሮግራሞች፣ በምዘናዎች፣ በማጠናከሪያ ፕሮግራሞች፣ በግራፊንግ፣ ወዘተ... ላይ ፈተና መፈተን ይቻላል። ማንኛውም ከ ዓ.ባ.ቴ የ40 ሰዓት ሥልጠና የተገኘ ክህሎት ክትትል እስከተደረገበት ለእጩ ክህሎት ፈተና ተቀባይነት ያለው የክህሎት ስብስብ ነው።

የሚመዘኑት ክትትል እየተደረጉ ያሉ አገልግሎቶች እና ክህሎቶች ናቸው። ለግምገማ የሚሆነውን ቅጽ የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቆጣጣሪው ነው።

- የእጩ ክህሎት ፈተና ቢያንስ ለ10 ደቂቃ የሚቆይ እና ቢያንስ 10 የክህሎት ስብስብ ክፍሎችን የሚሸፍን ፈተና መሆን አለበት።
- ቢያንስ 80% ትክክለኛ መሆን ያስፈልጋል።
- ሁለት የተለያዩ እጩ ክህሎት ፈተና ይፈለጋል።
- ለእያንዳንዱ የእጩ ክህሎት ፈተና የተለየ ችሎታ ያስፈልጋል።
- የእጩ ክህሎት ፈተና ልክ እንደ የሕክምና ታማኝነት ግምገማ አይነት እዛው በእዛው እጩው የአገልግሎት አቅርቦት ሲሰጥ የሚገመግም ነው።

እንደ ማንኛውም የክትትል መስፈርቶች፣ የእጩ ክህሎት ፈተና ዎች ተቆጣጣሪው በአካል ባለበት፣ አሊያም በርቀት ለምሳሌ በHi Rasmus፣ Zoom፣ Facetime፣ ወዘተ፣ ወይም ደግሞ በቪዲዮ ተቀርጾ ሊወሰዱ ይችላሉ።

# የእጩ ክህሎት ፈተናን ለሚያዘጋጀው ተቆጣጣሪ

የእጩ ክህሎት ፈተና የመረጃ መሰብሰቢያ ሉክ ለመፍጠር እነዚህን መመሪያዎች ተከተሉ፡-

- የሚገመገመው አገልግሎት ወይም የክህሎት ስብስብ የትኛው እንደሆነ ይወስኑ።
- ለተመረጠው ክህሎት የተግባር ትንተና ወይም የእርምጃዎች ዝርዝር ይፍጠሩ።
- ከክህሎቱ ለመገምገም የሚፈለጉ ቢያንስ 10 ነጥቦችን ይፍጠሩ።
- የውጤት አሰጣጥ ስርዓት ይፍጠሩ (አዎ/አይ፣ +/-፣ ወዘተ.)
- እጩው የተመረጠውን ክህሎት በማሳየት ላይ ሳለ የአፈጻጸሙን ውጤት ይስጡ።

የእጩው ተቆጣጣሪ የእጩ ክህሎቶችን መፈተሻ ማጽደቂያ ቅጾችን ወደ ተቆጣጣሪው መለያ ማስገባት ይጠበቅበታል።



# የእጩ ክህሎት ፈተና መረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ ምሳሌ



ቀን፡- ___________________ እጩ፡-______________________________ ተቆጣጣሪ፡- _____________________

የተጀመረበት ሰዓት፡- ______________ የተጠናቀቀበት ሰዓት፡- _____________ የጊዜ ርዝመት፡- _______________

| | ሙከራ 1 | ሙከራ 2 | ሙከራ 3 | ሙከራ 4 | ሙከራ 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| ቁሳቁሶች ተዘጋጅቷል | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ |
| የተማሪ ትኩረትን ይስባል | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ |
| ኤስ.ዲ (SD) ያሳያል | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ |
| ተማሪው እንዲመልስ 5 ሴኮንድ ይጠብቃል | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ |
| ትክክለኛውን ምላሽ ያጠናክራል | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ |
| ስህተት ከሆነ ኤስ.ዲ (SD) እና ቀጣዩን ፍንጭ ያሳያል | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ |
| ቁሳቁሶችን ያነሳል | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ |
| መረጃን ይመዘግባል | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ |
| ለቀጣይ ሙከራ ያደራጃል | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ |
| የመሃል ሙከራ ባህሪን ያስተዳድራል | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ | አዎ/አይ |
| | /10 | /10 | /10 | /10 | /10 |

በዚህ ለልዩ ሙከራ ፈተና የሚሆን የእጩ ክህሎት ፈተና ምሳሌ፥ ተቆጣጣሪው በ5 ሙከራዎች ውስጥ ለ10 የተለያዩ ክፍሎች የያዘ እጩ ክህሎት ፈተና ይፈጥራል። እጩው ሙከራዎችን በመተግበር ላይ እያለ፥ ተቆጣጣሪው የእጩውን የትግበራ ትክክለኛነት ይገመግማል። በዚህ ምሳሌ ውስጥ ላለው ለባለ አምስት ሙከራ የእጩ ክህሎት ፈተና እጩው ለእያንዳንዱ የሙከራ ክፍል አዎ ከሆነ አዎ፥ አይ ከሆነ ደግሞ አይ የሚለውን ያከብባል። አስተውሉ፥ ይህ ምሳሌ እንድታዩት በሚል ብቻ ነው የተሰጠው። እያንዳንዱ የእጩ ክህሎት ፈተና ቢያንስ 10 ደቂቃ ያህል መርዘም አለባቸው። ለአንዳንድ የDTT ክፍለ ጊዜያት 10 ደቂቃ ማለት ለአንዳንድ ተማሪዎች ወደ 20 ሙከራ ይጠጋል።

# የእጩ ክህሎት ፈተና ማጽደቂያ ቅጽ

ቀን፡-____________________ እጩ፡- ________________________________________

ተቆጣጣሪ፡- ________________________________________

የእጩ ክህሎት ፈተና ዝርዝር፡- ________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

የእጩ ፊርማ፡- ________________________________________

የተቆጣጣሪው ፊርማ፡- ________________________________________

ለእያንዳንዱ እጩ ክህሎት ፈተና አንድ ቅጽ ይሙሉ። ሁለት እጩ ክህሎት ፈተናዎች ያስፈልጋሉ። የሁለቱም የእጩ ክህሎት ፈተናዎች በተለያዩ የክህሎት ስብስቦች ላይ መሆን አለባቸው። የእጩው ተቆጣጣሪ የእጩውን የክህሎት ስብስብ መንደፍ፣ መምራት እና ማጽደቅ (አልፏል/አላለፈም) ይጠበቅበታል። ተቆጣጣሪው የተሞላውን ቅጽ ወደ ራሱ መለያ እንዲያስቀምጥ ይጠበቅበታል። ለሁለቱም ለተሰጡጥ የእጩ ክህሎት ፈተናዎች ቅጽ ያስፈልጋቸዋል። ተቆጣጣሪው በበቂ ሁኔታ አልተከናወነም ብሎ ፕሮጀክቱን ከገመገመ ለዚያ ፕሮጀክት ቅጽ አያስፈልገውም። ሁለት እጩ ክህሎት ፈተናዎች በአጥጋቢ ሁኔታ እስኪያልፉ ድረስ የሚፈተኑትን የፈተናዎች ብዛት ላይ ምንም ገደብ የለም።

የተረጋገጠ ዓ.ባ.ተ ለመሆን ዋና ከሆኑ የጉዞ ክፍሎች በሙያው ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ትምህርትን ማሻሻል እና ሙያን ማዳበር ነው። ማረጋገጫ ከመሰጠጡ በፊት 4 ሰዓት በትምህርት ማሻሻያ ማሳለፍ ያስፈልጋሉ።

እያንዳንዱ እጩ ያገኘውን የቀጣይ ትምህርት አሀዶች በሰነድ መመዝገብ ይኖርበታል። ሰነድ ስናዘጋጅ ያ ሰነድ የሚቀመጥ ሆኖ የሥልጠናው ይዘት እና ርዝመት፣ ሥልጠናው መቼ እንደተሰጠ፣ እና ሥልጠናው የተሰጠው በማን እንደሆነ በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት። የሚከተሉት የቀጣይ ትምህርት አሀዶች ተቀባይነት አላቸው፡-

- በዓ.ባ.ተ ወይም ከባህሪ ትንተና ጋር በተገናኘ መረጃ በኦንላይን ወይም በአካል ሴሚናሮችን፣ ዎርክሾፖችን ወይም ስልጠናዎችን መሳተፍ
- ስለ ዓ.ባ.ተ ወይም የባህሪ ትንተና ነክ መረጃዎች በሴሚናር፣ በዎርክሾፕ ወይም በስልጠና ማቅረብ


# ቅድመ-ዕውቅና የቀጣይ ትምህርት አሀዶች

- 4 የቀጣይ ትምህርት አሀዶች ያስፈልጋል።
  - 1 ሰዓት በሥነ ምግባር
  - 1 ሰዓት በባህላዊ ብዝኃነት እና ንቃት
  - 2 ሰዓት በዓ.ባ.ተ ርዕሶች

ሁሉም መስፈርቶች ሲሟሉ የዓ.ባ.ቴው እጩ የዓ.ባ.ቴ የኦንላይን ፈተናውን ተመዝግቦ ይፈተናል። የዓ.ባ.ቴ ፈተና መስፈርቶች የተዘጋጁት በዓለም ዙሪያ ያሉ እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች ብቃታቸውን እንዲያሳዩ ለማስቻል ነው።

- ምንም አይነት የፈተና ማዕከል አያስፈልግም።
- ወደ ተለያዩ አገሮች ጉዞ የለም።
- የአዳር ቆይታ ወይም ተጨማሪ ወጪዎች የሉም።
- ፈተናውን ለመውሰድ የሚያስፈልግህ ጸጥታ የሰፈነበት፣ ምቹ የሆነ የሥራ ቦታ እና ኢንተርኔት ብቻ ነው።
- የፕሮክተር እና የፈተና ደህንነት በመስመር ላይ ተጠናቅቋል።

# የዓ.ባ.ተ የፈተና ዝርዝር



- ፈተናው በኦንላይን፣ የፈተና ማዕከላት የሉም
- ኦንላን እና ቨርቱዋል ፈታኝ
- 75 የምርጫ ወይም የእውነት ወይም ሐሰት ጥያቄዎች
- ፈተናው በ3 ሰዓት መጨረስ አለባችሁ
- ይዘት፡- የዓ.ባ.ተ መሰረታውያን፣ ጉዳቶች፣ የማስተማር አይነቶች፣ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ስልቶች እና ሌሎች

ዓ.ባ.ቴ ሆነው ከተመሰከረላችሁ በኋላ፣ የእርስዎን ማረጋገጫ ለማስጠበቅ የተወሰኑ መስፈርቶች መሟላት አለባቸው። የተረጋገጠ የዓ.ባ.ቴ የምስክርነት ዑደቱ 2 ዓመት ነው።  ይህ ማለት አንዴ ካረጋገጡ በኋላ ያ ማረጋገጫ ለሁለት ዓመት ይጸናል። በየሁለት ዓመቱ ማረጋገጫውን ለማስቀጠል ድጋሚ የምስክርነት ሂደት ማድረግ ይኖርብዎታል።

## በየ 2 ዓመቱ እንደገና ማረጋገጫ ለማግኘት

- 8 የትምህርት ማሻሻያ አሃዶች (በየዓመቱ 4)
    - ሰዓት ሥነ ምግባር (በየዓመቱ 1)
    - ሰዓት በባህላዊ ብዝኃነት እና ንቃት (በየዓመቱ 1)
    - 4 ሰዓት በዓ.ባ.ተ ርዕሶች (በየዓመቱ 2)
- ቀጣይነት ያለው የዓ.ባ.ተ ልምምድ የተቆጣጣሪ ክትትል

## ትምህርት ማሻሻል እና ማሳደግ

እያንዳንዱ ዓ.ባ.ቴ ያገኙትን የቀጣይ ትምህርት አሀዶች በሰነድ መመዝገብ ይኖርበታል። ሰነዱ እንደ የተሳትፎ የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ የስልጠና ይዘት እና የጊዜ ርዝመት በግልፅ የሚያሳይ አካላዊ ሰነድ ያስፈልገዋል።

- በኦንላይን ወይም በአካል ሴሚናሮችን፣ ዎርክሾፖችን ወይም በዓ.ባ.ተ ወይም ከባህሪ ትንተና ጋር በተገናኘ መረጃ ስልጠናዎችን መሳተፍ ተቀባይነት አላቸው

- በሴሚናር፣ በዎርክሾፕ ወይም በዓ.ባ.ተ ወይም ከባህሪ ትንተና ጋር በተገናኘ መረጃ በስልጠና ማቅረብ

## ቀጣይነት ያለው ክትትል

- የሁሉም የዓ.ባ.ቴ ልምምዶች ብቃት ባለው ተቆጣጣሪ ክትትል ሊደረግበት ይገባል።
- ክትትል በአካል ወይም በርቀት፣ አንድ ግለሰብ ወይም በቡድን ሊሆን ይችላል በተጨማሪም 100% ቀጥተኛ ሊሆን ይችላል።
- የዓ.ባ.ቴ ተቆጣጣሪ በዓ.ባ.ቴ.ድ መመዝገብ እና የተቆጣጣሪ መስፈርቶችማሟላት አለበት።
- ከአንድ በላይ ተቆጣጣሪ ይፈቀዳል
- በቅድመ-ዕውቅና የማረጋገጫ ክትትል ወቅት ቅጾቹ በተፈለጉበት ትክክለኛ መንገድ ለእያንዳንዱ የክትትል ስብሰባ የክትትል ሰነድ ቅጽ ያስፈልጋል።

ዓ.ባ.ተ.ድ  የዓ.ባ.ቴ አገልግሎት አቅርቦትን በተመጣጣኝነት ቢያንስ ለእያንዳንዱ 40 ሰአታት ልምምድ l ሰዓት ክትትል እንዲደረግ ይጠይቃል



*<u>ለእያንዳንዱ የ40 የልምምድ ሰዓታት ከl ሰዓት በላይ በተቆጣጣሪ ክትትል የሚደረግ ልምምድ</u> ቢሆን መልካም ተሞክሮ ሆኖ ተገኝቷል። በእያንዳንዱ በ4-5 ሰዓት አዳዲስ ክህሎቶችን በሚማርበት ጊዜ፣ አዲስ ታካሚ መከታተል በሚጀምርበት ጊዜ ወይም አዲስ የምስክር ወረቀት ሲያገኝ l ሰዓት በተቆጣጣሪ ክትትል የሚደረግ ልምምድ ሊየስፈልገው ይችላል። <u>ለ 40 ሰአታት ልምምድ የአንድ ሰአት ክትትል አስፈላጊነት ፍፁም ነው።</u> ዝቅተኛ እና ትክክለኛዎቹ መጠኖች በዓ.ባ.ቴተቆጣጣሪው በክሊኒካዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት በሚወስኑት መሰረት ከፍ ያለ መሆን አለባቸው።*

-